# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## የይዞታና የንብረት ባለቤትነት
## መብት ያለገደብ ይከበር!!

ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም

የመለስ አገዛዝ የከተማን ቦታ በሊዝ የመያዝ አዲስ አዋጅ ደንግጎ በጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም. ይፋ ካደረገ በኋላ በሱና በደጋፊዎቹ መካከል ንትርክ ያስከተለ መሆኑ እየተስተዋለ ነው። የመለስ አገዛዝ ግን የአዋጁን ጉድለትና ይዘት ተንትነው እርምት እንዲደረግ ባላቸው አቅም የጣሩትን ክፍሎች ያው የተለመደ የኪራይ ሰብሳቢ ጩኸት ነው በማለት በማጥላላትና አግባብነት የሌለው ትችት እየሰጠ አምባገነንነቱን በአደባባይ ያወጣበት ሁኔታም በግልጽ ታይቷል። ሆኖም በአዋጁ ላይ እየቀረቡ ያሉ ትችቶች ግለታቸውና ይዘታቸው እየጨመረ ሄደ እንጂ ሊቀንስና ሊረግብ አልቻለም። እንዲያውም የሕዝብም ቁጣና የከረረ ተቃውሞ ታክሎበት ገለጻና ማብራሪያ እንዲሰጡ የግድ ያላቸው ሁናቴ ባላሰቡትና ባልጠበቁበት መልኩ ተከሰተ።

ሰሞኑን ስለዚሁ ህገወጥ እርምጃ እናስረዳለን ብለው የጣሩትን ቱባ ቱባ የወያኔ ባለሥልጣኖችና ካድሬዎች የአዲስ አበባ ሕዝብ ሌባ ሌባ ብሎ በመኮንን አዋርዶ መመለሱ ለሕዝብ ተቃውሞ በቂ ማስረጃ ነው። የመለስ አገዛዝ የሕጉን ይዘት ግልፅ ለማድረግ የላካቸው ባለሥልጣናቱ ያልለመደባቸው ነበርና ጥራት በመስጠት ፈንታ ይበልጡኑ በማመሰቃቀላቸው ግርታ መፍጠሩም በሚገባ ታይቷል። በተለይም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ለሕሊናቸው ተገዢ የሆኑ ዜጎች ሕጉ የባሌበትነት መንፈስን የሚደፈጥጥ፤ ለእድገት አስፈላጊ የሆነው አስተማማኝ ሁኔታን ጨርሶ የማይፈጥር፤ ቀድሞውኑ መብታቸው የተገፈፉ ዜጎችን ይበልጡኑ በጠበቀ ሕግ የአገዛዙ ጭሰኛ ለማድረግና በሊዝ ክፍያ የሕዝብን ሀብት ለመዝረፍ ያመቻ ዘንድ የተወጠነ ሴራ መሆኑን በማብራራት ተቃውሟቸውን ግልፅ አድርገዋል። የተሻለ የመሬት ስሪትና አስተዳደር ሊፈጠር የሚችለውም አገዛዙ ከሥልጣን ተባርሮ የሕዝቡን የልብ ትርታ ሊያዳምጥ የሚችል ሕዝባዊና ፍትሓዊ አስተዳደር ሲመሰረት እንደሆነም አፅንዖት በመስጠት ገልፀዋል። ለዚህም ሕዝብ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ ማቅረባቸው ታይቷል፤ ተነቧል፤ ተሰምቷል። በተለያዩ ቦታዎች በተደረጉት ውይይቶችም መሰል አስተያየቶች ተንፀባርቀዋል። በዚህም የተነሳ ለአገዛዙ የሳሳ ልብ ያላቸው ደጋፊዎቹ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ በበኩላቸው የት እንደሚደርስና ምንስ እንደሚያስከትል በመገንዘባቸው ከወዲሁ የእርምት አቤቱታና የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ለሕዝብ ገለፃ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ ጥሪ ማቅረባቸው ተስተውሏል። ቅቤ የማይወጣው ወተት መናጥ ሆነና ነገሩ እምብዛም የሚያስኬዳቸው አልሆነም።

በተደረጉት ጥቂት ስብሰባዎች ሕዝብን ሳያማክሩ ሕጉን ማውጣታቸው ግድፈት መሆኑን ለመቀበል ዳዴ ቢሉም አገዛዙ በግትርነቱ ቀጠለበት እንጂ ማንነቱን ሊቀይር ጨርሶ የማይፈልግ መሆኑ በድንፋታው ግልፅ አድርጓል። በሕጉ ውስጣዊ ይዘት የተነሳ ግን የተከሰተው ውዥንብርም በድንገት ተኖ ሊጠፋ አልቻለም። ይህንን ሁናቴ ቀደም ብሎ የተገነዘበው ሕዝብ በበኩሉ ለአገዛዙ ያለውን ተቃውሞ በግልፅ በማሳየቱ ፍላጎቱ ምን እንደሆነ በአደባባይ ይፋ አድርጓል። ቀጣዩ እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚገባም ግልፅ የተደረገበት ክስተት ሊሆን ችሏል። ሕዝብ በውስጡ ያለውን እምቅ ኃይልም አንፀባርቆበታል።

በተደጋጋሚ እንደተደመጠውና እንደተገለፀውም ለሕጉ መውጣት አወናባጅ በሆኑ "ከመሬት ጋር በተያያዘ ሙስና በመስፋፋቱ የኪራይ ሰብሳቢን ፖለቲካል ኤኮኖሚን በር ለመቀርቀር፤ ዋናው አላማው ለሕዝብ የሚጠቅም የመሬት አስተዳደር ሥርአት ለመገንባት"፤ የሚሉ አነሁላይ አረፍተ ነገሮች በየንግግራቸውና መጣጥፎቻቸው እየሸነቆሩ በማጠየቂያነት ባቀረቡበት አንደበታቸው አምባገነነታቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ አዋጁን ከማስፈፀም ወደኋላ አንልም የሚልና መሰል ቀጭን የወታደራዊ ማስፈራሪያ ዛቻ መወርወራቸውም ተስተውሏል። ተነቧል። ዋናው የኪራይ ሰብሳቢ ፈጣሪ አገዛዙና ሥርአቱ፤ ዋና ተጠቃሚዎችም የአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች መሆናቸውን ለመሸፈንና ለአዋጁ መውጣት ምክንያት በማለት ያቀረቡት ማጠየቂያ ውሃ የማይቋጥር እየሆነባቸው መምጣቱ ሕዝብ የቁጣ ጅራፉን እያሰማ መሳለቂያ እያደረጋቸው ይገኛል።

ከሁሉ በላይ አስገራሚው፣ ይህ አዋጅ ይፋ ከተደረገ በኋላ በራሱ ያልተሟላ መሆኑ በተደረጉት የእሰጥ አገባ ውይይቶች ግልፅ ሲደረግ፤ ይህንን ለማስተባበል አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ደንብ፣ ያፈጻጸም መመሪያ (ማኑዋል) ወደፊት በቀጣይነት ይወጣል በሚል ለመሸፋፈን የተደረጉት ጥረቶች እንኳን የኢትዮጵያን ሕዝብ የራሱን አባላትና ደጋፊዎች ሊያሳምን ያልቻለ መሆኑ በሚገባ ተንፀባርቋል። በዚህም የተነሳ ነው አዋጁን ተግባራዊ ከማድረግ ምንም አያግደንም የሚል ማስፈራሪያ ተሰጥቶ የተደመጠው። ለዚህም ነው ቀድሞውኑ ሕዝብን ብታማክሩ የሚለው አቤቱታ በባለሥልጣናቱ ዘንድ እምብዛም ውጤት የሚያስገኝ ባለመሆኑ በሕዝብ ዘንድ ትኩረትና ግምት ያልተሰጠው። የአገዛዙን የግብር ውጣ አሠራርና ተግባር በሚገባ ለሚያውቅ ሕዝብን ቀርቶ የሚመለከተውን ምክር ቤት ተብዬ እንኳን በሚገባ ላለማማከር ተብሎ በምክነያትነት የተሰጠውን ለ“ትራንስፎርሜሽኑ“፣ ማለትም ለለውጥ ተብዬው እቅድ መሳካት ካለው ጠቀሜታ አንፃር የሚለው ይህንኑ አመላካች ነው። ይህ ሁናቴ ከግምት ሲገባ በርግጥም አቤቱታ ማቅረቡ ዋጋ ቢስ ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ነቢይነትን አይጠይቅም። አገዛዙ ምንም ቁጥጥር የሌለበት፤ የማንአህሎኝነቱንና የአምባገነን ጠባዩን በአደባባይ በግልፅ ያንፀባረቀበት ክስተት እንደሆነ በራሱ በድርጊቱ አስመስክሯል። ታዲያ ይህንን አገዛዝ ለመማፀን መሞከር የራስን ጀርባ በካድሬዎቹ ለማስረገጥ መመቻቸትና መጃጃል ከመሆን በምን ይለያል? ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ኃይሎች ይህንን አጥብቀው ይቃወሙታል እንጂ ሊያስተናግዱት ከቶም አይጠበቅባቸውም።

የመለስ አገዛዝ በአዲስ አበባ የተወሰኑ ካድሬዎችንና ዝቅተኛ ባለሥልጣናትን ያጠቃለለና ገለልተኛ ተብለው ለሚገሙቱ ጭምር ያደረጋቸውን የይስሙላ ውይይቶች በራሱ ሙሉ ቁጥጥር በሚገኘው የዜና ተቋማት በማራገብ ሕዝብን ለማደናገር ያደረገው ጥረት የደረሰበትን ሽንፈት በሚገባ አጋልጦበታል። የሕዝብ ፍላጎቱ መሬትና መብት አልባ የሚያደርገውን ሕግ አገዛዙን በመለማመጥ ከሕጉ ውስጥ ይህ ይውጣ፤ ያ ይግባ፤ እያለ አቤቱታ የሚያቀርብበት ምንም ምክንያት የለውም። የመለስ አገዛዝ ሥልጣን በያዘበት የመጀመሪያዎቹ አመታት ትምህርትና ልቦና እንዲያገኝ በቀና በማሰብ ከሕዝብ በኩል የተደረጉ በርካታ ጥረቶች ውጤት ያላስገኙ ብቻ ሳይሆኑ በፈሪነትና የደካማ ምልክት ተደርገው መወሰዳቸውን ሕዝብ የሚረሳው አይሆንም። ምን ታድርጉኛላችሁ የሚለው እብሪቱን ይበልጥ ማጠናከሩን ምክርን ሰሚ መሆን ክብረ ነክ አድርጎ መቁጠሩንም የምናስታወሰው ነው። እንዲያውም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ያለውን ንቀትና ጥላቻ በተጠናከረ መልክ መቀጠሉን በተከታታይ ለምክር ቤት ተብዬው በቁጣና በድንፋታ የተደረጉ ንግግሮችም በቁጭትና በሀዘን የታዘነብናቸው ናቸው። በመሆኑም ሕዝብ አሁን በወጣው አዲስ የሊዝ አዋጅ ምክር በመስጠት የሚያገኘው ጥቅም ቢኖር የንብረት ብሎም የሀገር ባለቤትነት ማጣትና ለፍቶ

ጥሮ ግሮ ከሚያገኛት ገንዘብ በሊዝ አማካኝነት በአምባገነኖች መነጠቅ፤ በሀገሩ ሀገር የለሽ እየሆነ ራሱንም ቤተሰቦቹንም ለከፋ የኑሮ ሁናቴና ብዝበዛ መዳረግ ነው። ይህ እንዲሆን መፍቀድ ሕሊናው አይቀበለውምና አገዛዙን ከሥልጣን ሊያወርድ በሚችልበት መስከ መሰማራቱ አማራጭ እንደሌለውም በመገንዘቡ ይህንን እርምጃውን ለማሰናከል የሚጥሩትን በሙሉ እንዳመጣጣቸው ይታገላቸዋል። በቅርቡም በተለያዩ አካባቢዎች የታየውም ይኸንኑ ጠቋሚ ነው።

አዲሱ የሊዝ አዋጅ መሻሻል ተደርጎበት የወጣ ነው ቢባልም አገዛዙ የሕዝብን መብት ነጥቆ መሬትን በራሱ ሙሉ ባለንብረት በማድረጉ አሁንም ካለፈው ያልተሻለ እንዲያውም በሰፋ ሁኔታ ለሙስና ዝርፊያ ለአባላቱና ካድሬዎቹ የተመቻቸ ነው። መልካም አስተዳደር ሊገነባ ባለመቻሉ፤ "ግልፅነትና ተጠያቂነት" ባፍ መነገር ብቻ ሳይሆን በየመሥሪያ ቤቶች ለላንቲካ በየግርግዳዎች ተለጥፈው ያሉ ቢሆኑም አዲሱ ሕጋቸውን ከሙስና የሚያጸዳው እነሱንም በድንገት ፃዲቅነት የሚያላብስ አይሆንም። ሙስናን ለመዋጋት ተብሎ የወጣው ሕግ ተራውን ሕዝብ እንጂ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናቱን የሚቀጣና ወደ እስር ቤት የሚወስድ አይደለም። ይህ አዋጅ በግልፅ ያሳየው አንድ ነገር ቢኖር በሥልጣን ላይ የተቀመጡት ግለሰቦች በችሎታቸው ወይንም ደግሞ በተመክሮ ባካበቱት እውቀታቸው ሳይሆን ለአገዛዙ ባላቸው የካድሬነት አገልጋይነት ነው። የመገንዘብ አቅም የሌላቸው ሕዝብን ለማገልገል ሳይሆን ሕዝብ እነሱን እንዲያገለግል በጫንቃው ላይ የተቀመጡ ናቸው። በድፍረት ተናጋሪና አዋቂ ለመምሰልና ደካማነታቸውንም ለመሸፈን ቢጥሩም ያወጡትን ሕግ እንኳን ባግባቡ ግልፅ ለማድረግ ያልቻሉ ለመሆናቸው የውይይት ሂደቱ  አጋልጧቸዋል።

ይህ የንብረትና የሀገር ባለቤትነትን መብት የሚያሳጣ ሕግ እንደ ሌሎቹ ሕጎች ሁሉ ለሕዝብ ሳይሆን በሕዝብ ላይ እንዲጫን የተቀመረ ነውና ማንም ሀገር ወዳድ አጥብቆ የሚቃወመው ነው። የሀሳብና የፍላጎት መንሸራሸርና መግባባት ሳይሆን ጠመንጃ ሕግ በሆነበት ሀገር የሚጠበቅ ነውና የሚያስደንቅ አይሆንም። ሕገወጥ አገዛዝ እንዳሻው ሕገወጥ የሆነ አዋጅ፣ ሕግና ደንብ፣ የሥራ ደንብ (ማኑዋል) እያለ መቀለዱን፣ መቀላመዱን ማስቆም የግድ ይላል። የመለስ አገዛዝ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው እያለ እያደናገረ ራሱን ብቸኛ የመሬት ባለቤትና እንዳሻው አዛዥ ናዛዥ ማድረጉ፤ መሬትን ለባዕዳን እንዳሻ መቸብቸቡ በሚገባ ተወግዶ በምትኩ መሬት በመንግሥት፣ በማህበረሰቡና በግለሰብ ባለቤትነት መረጋገጥ ይህንንም የሚያስከብር ሕግ መኖር የግድ ነው። ሕዝብ በመለስ አገዛዝ የተነጠቀውን የሀገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን በጁ ማስገባት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ በቅድሚያ ይህንን አገዛዝ ማስወገድ አማራጭ የሌለው ነው። በመሆኑም አዲሱ ሕግ ተቀባይነት ሊኖረው ጨርሶ አይገባም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግሌ የሚለው ይዞታና ንብረት የማፍራት ብሎም ለፈለገው የማውረስ፣ የመሸጥ፣ በወለድ አግድ የማስያዝ መብቱ ያለምንም ገደብ ካልተከበረለት ዞሮ ዞሮ በታሪክ አጋጣሚ ከሥልጣን ለሚቆናጠጡ አገዛዞች ጭሰኛ ያደርገዋልና ይህንን ከወዲሁ መቃወም ተገቢ ነው። የመለስ አገዛዝ ሊወድቅ እየተንገዳገደ ያለ ነው። ገፍቶ መጣል የህዝብ ጉዳይና የጋራ ትግል ውጤት ነው - ሕገ ወጥ የሆነ አገዛዝ የሕዝብን ፍላጎት የማያንፀባርቁ ሕጎች የማውጣት ዘመኑ ለአንዴም ለሁሌም እንዲያከትም ማረግ የሁሉም ግዴታ ነውና።

የሕዝብን ሉአላዊነት የሚፃረር ሕግ ይወገድ!!
በትግል የሕዝብ ሉአላዊነት ይከበር!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France